# ስለ ኢትዮጵያ
# ጥቅምት 2016 ዓ.ም

**አብይ አህመድ ሀገራችን ኢትዮጵያን ገደል ለመክተት በከፍተኛ ፍጥነት እየተንደረደረ ነው ።። ነገ ዛሬ ሳይባል የመንግስት ሃላፊነቱን በሀገር አቀፍ የምክክር ሸንጎ ለሚታቀፍ የሽግግር መንግስት ማስረከብ አለበት ።። ኢትዮጵያን እንደሀገር ለማስቀጠልና ሕዝቡን አሁን ከሚታየው የባሰ እልቂት ለማዳን ሌላ አማራጭ የለም ።። በአንድ ወፈፌ አምባገነን ማን አለብኝነትና የጥፋት ውርጅብኝ ኢትዮጵያን የሚያክል ሀገር ሊፈርስ አይገባም ።።**

የሀገራችን ሕዝብ ፡ አእምሮው የታወከ ፍፁም ጨካኝ አምባገነን የሀገር መሪ ነኝ ባይና ፡ እሱ ሥር በተኮለኮሉ አሽከሮቹ ፡ ለከት የለሽ የሥልጣንና የዘረፋ ፍላጎት ፡ ሥር የሰደደ ክፋትና የማያቋርጥ የደም ጥማት የተነሳ ፡ ዛሬም እንደገና በጦርነት እሳት እየተለበለበ መሆኑ እጅግ ያሳዝናል ፡ ልብ ያቆስላል ።።

ባለፉት አምስት አመታት በተካሄዱት ፍፁም አላስፈላጊ የእርስበርስ ጦርነቶችና የሰላማዊ ዜጎች አሰቃቂ ጭፍጨፋዎች ፡ በመላው ኢትዮጵያ በከንቱ የፈሰሰው ተሰፍሮ የማያልቅ የምስኪን ሕዝብ ደምና ፡ የወደመው የሀገርና የሕዝብ ንብረት ፡ በዚያም ሂደት የደበዘዘው የአብሮነት እሴት ያነሰ ይመስል ፤ የመንግስት ሥልጣን በያዙ ጥቂት ጨካኝ ግለሰቦችና ቡድኖች እኩይ ዓላማና ማንአለብኝነት የተነሳ ፡ ሀምሳ አመት ሙሉ እፎይታ ያጣው ሕዝባችንና ድሃ ሀገራችን ፡ እንደገና ሌላ ዙር ጦርነት ውስጥ መነከራቸው የግፍ ግፍ ነው ።።

ላለፉት ሠላሳ ሁለት አመታት ካለቃጢያቱ ካላንዳች ተከላካይ ባለማቋረጥ ሲቀጠቀጥ የኖረውንና ፡ ይብሱንም ባሁኑ አምባገነን የአምስት አመት የሥልጣን ዘመን ፡ በሚልዮኖች ሲፈናቀልና በሺዎች ሲታረድ የኖረውን ፍፁም ድሃ አማራ ኢትዮጵያዊ ወገኑን ለመፍጀት ፡ “የሀገር መከላከያ ሠራዊት" ሲሰለፍ ማየት ፡ ማንኛውም ሰው የሆነ ፍጡር ሊሸከመው ከሚችለው ሃዘን በላይ ነው ።።

የሰው ልጅ ደምና እንባ ወንዝ ሆኖ ቢፈስ ፡ በክፉዎችና በደንቆሮዎች ሥራ ምክንያት ፡ በኢትዮጵያ ምድር ላይ ካለማቋረጥ እየወረደ ያለው የደምና የእንባ ጎርፍ ፡ ዓለምን ያጥለቀልቅ ነበር ።።

አለመታደል ሆኖ ፡ ላለፉት ሃምሳ አመታት ፡ በኢትዮጵያ የመንግስት ሥልጣን ላይ በተከታታይ የሚቀመጡ ሰዎችና ጋሻ ጃግሬዎቻቸው ፡ ይህንን ለማሰብና ፡ ለሕዝብ ሰላምና የኑሮ መሻሻል ቅድሚያ ለመስጠት የሚፈልጉም የሚችሉም ሰዎች አይደሉም ።።

ያሁኖቹም መሪዎች ፡ ከመልካምነት ከእውቀትና ከብስለት ፍፁም ነፃ በሆነው የእውር ድንብር የሥልጣንና የዘረፋ ጥማታቸው የተነሳ ፡ ሀገሩን በማያባራ ሁከትና ጦርነት ማጋየትን እንደ ጀብዱ የሚያዩ ፡ የሰይጣን ሥራቸውን ጥቁሩን ነጭ ነው እያሉ ካለምንም ሃፍረት በአደባባይ የሚለፍፉ ፡ በሕዝብ ላይ ካለማቋረጥ የሚያላግጡ አይንአውጦች ናቸው ።።

በዚህ በማያባራ የእብዶች ሆያሆዬ : ካለኃጢያቱ በደመከልብ የሚያልቀው ድሃ ሕዝብና : እየወደመ ያለው ሀገር : ለነዚህ በክፋትና በጭካኔ ለታወሩ ሰዎች ምናቸውም አይደለም ::

ለከትየለሽ በሆነ የሥልጣንና የዘረፋ ፍላጎት ከመታወራቸው ብዛት : ራሳቸው ቤተሰቦቻቸውና ልጆቻቸው የቆሙበትን መሬት እየደረመሱት መሆናቸውን ማመዛዘን አይችሉም ::

ትናንት በሕወሃት አልጠግብ ባይነትና ክፋት ምክንያት በተካሄደው እጅግ አሰቃቂ ጦርነት : እንደቅጠል የረገፈው ከሚልዮን በላይ የሚገመት ድሃ ሕዝብ : ወታደር ሚሊሽያና እጅግ ብዙ ንፁሃን ዜጎች : ሴቶች ሕፃናትና አረጋውያን ሬሳ የአውሬ ሲሳይ ሆኖ ቀርቷል ::

በጦርነቱ ሂደት : በትግራይ በጎንደር በወሎ በጎጃም በአፋር በሰሜን ሸዋ : በሰላማዊ ዜጎች ላይ በሰፊው ለተፈፀመው እጅግ አሰቃቂ ወንጀል ማንም ተጠያቂ አልሆነም ::

የሀገሩ ኢኮኖሚ በጦርነትና በአጠቃላይ የአመራር ብልሹነት የተነሳ ገደል ገብቶ : ሕዝቡ ግዙፍ ችግር ላይ ከወደቀ ከርሟል :: በሀገራችን ታሪክ ለመጀመርያ ግዜ ለመንግስት ሠራተኞች ደሞዝ ለመክፈል የሚያቅትበት ደረጃ ላይ ተደርሷል ::

በየክፍለሀገሩ በዘሩና በቋንቋው ምክንያት ብቻ የተጨፈጨፈውና በሚልዮኖች የተፈናቀለውን : ዛሬም ድረስ ካለምንም ምክንያት ዘሩ ብቻ እየተመረጠ የሚባረረውንና የሚገደለውን ሕዝብ እግዚኦታ የሚሰማ የመንግስት ጆሮ ወይም የፍትህ አካል በጭራሽ የለም ::

የሰሜኑ ጦርነት በድርድር መቆሙ ተመራጭነት እንደተጠበቀ ሆኖ : በዚህ ፍፁም አላስፈላጊ : እጅግ አሰቃቂና አውዳሚ ጦርነት ቀንደኛ ተዋናይ የነበሩትና : ያንን ሁሉ ምስኪን ሕዝብ ያላንዳች ርህራሄ በገፍ የፈጁትና ያስፈጁት የሕወሃት መሪዎች : ተጠያቂ ሊሆኑ ቀርቶ : ሁለት አመት ሙሉ ያን ሁሉ ደሃ ወታደር እያስጨረሱ ሲዋጉዋቸውና : በቀን 24 ሰዓት ጥንብ እርኩሳቸዉን እያወጡ ሲወነጅሏቸው በነበሩት የ"ብልፅግና" መሪዎች : በአደባባይ ጉንጫቸዉ ተገላብጦ ተስሞ ካባ ተሸልመዋል :: በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገር እንዳሻቸው እንዲጎማለሉ ተፈቅዶላቸዋል ::

አሁን በቅርቡ ደግሞ : EFFORT በሚባል ስም የሀገሪቱን አንጡራ ሀብት ለ27 አመት ሙልጭ አርገው የዘረፉበት ግዙፍ የቢዝነስ ተቋም : ሥራውን (ዘረፋውን) እንዲቀጥል በይፋ ተፈቅዶለታል ::

አብይ አህመድ ይህንን የጉድ ጉድ በፍፁም አይንአውጣነት በይፋ ሲፈፅም : ትናንትና በራሱ አንደበት በተደጋጋሚ : "የሰሜን እዝ በጁንታው በሕወሃት ከጀርባው ተወጋ : በተኛበት ተረሸነ : ሬሳው እንደ ውሻ መሬት ለመሬት ተጎተተ : ሴት ወታደሮች ጡታቸውን ተቆረጡ በሳንጃ ተዘለዘሉ : በሺዎች የሚቆጠሩ ወታደሮችና መኮንኖች ልብሳቸውን ተገፈው ራቁታቸውን ተባረው ኤርትራ ገቡ: ሌላም ሌላም አሰቃቂ ግፍ ተፈፀመባቸው..." እያለ ሌት ተቀን ሲንተከተክ እንዳልነበር ሁሉ : የሕወሃት ወንጀለኞችን ለፍርድ ማቅረቡ ለግዜው ይቆይ ቢባል እንኳን : ይህን ያህል አይን አውጥቶ

በአደባባይ ሲሸልማቸው : ያ ሁሉ ዘግናኝ ግፍ የተፈፀመባቸው ወታደሮችና ወገኖቻቸውስ ሕዝቡስ ምን ይለኛል ሊል የሚችልበት አእምሮና ህሊና የሚባል ነገር ጨርሶ የሌለው ሰው መሆኑን ሁነኛ ማሳያ ነው ::

በአንፃሩ ደግሞ በዚያ አውዳሚ ጦርነት ካለ አንዳች የመንግስት የስንቅና ትጥቅ እገዛ : በራሱ አሮጌ መሳርያና : የአብይ መንግስት ማርከህ ታጠቅ ባለው መሰረት : በከፍተኛ መስዋዕትነት እየማረከ : የሕወሃትን እስከአፍንጫው የታጠቀ ጦር በቀዳሚነት የመከተውና : አብይን እና ጋሻ ጃግሬዎቹን ሕወሃት በይፋ ከደገሰላቸው በአደባባይ መቀፍድድ ያዳነው : በኢትዮጵያዊነቱ የማይደራደረው የአማራ ፋኖ ሕዝባዊ ኃይል : ካለምንም ቅድመ ሁኔታ ባስቸኳይ ትጥቅህን ካልፈታህ ተብሎ : በአብይ መንግስት ይፋ ጦርነት ከታወጀበት ወራት አስቆጥሯል :: በዚህም የተነሳ በሸዋ በጎንደር በጎጃም በወሎ ሰፊ ውጊያ እየተካሄደና እጅግ ብዙ ሕዝብ እንደገና እያለቀ ነው ::

ፋኖ የሚባለው የአማራ ሕዝባዊ ኃይል ተጠሪዎች : ለምን መንግስት ባዘዘው መሰረት ትጥቃችሁን አትፈቱም ሲባሉ የሚሰጡት መልስ ግልፅና ትክክለኛ ነው ::

- አሁን ባለው የጎጥ ሕገመንግስት የአማራ ክልል በሚባሉት ክፍላተሃገር : ሕዝቡን በጭካኔ የፈጀውና : ዘመን የማይሽረው ወንጀለኛ የሆነው ሕወሃት : ትጥቁን መፍታት ቀርቶ : በየእለቱ እንደገና የሚጠናከርበት መንገድ እየተመቻቸለት እያለ :

- ከሕወሃት የግፍ አገዛዝ በብዙ የሕይወት መስዋእትነት ወደቀድሞ ይዞታቸው የተመለሱትን የወልቃይትና ራያ መስተዳድሮች እንደገና ለመንጠቅና : ሕዝቡን እንደቀድሞው ለመርገጥ : በአብይ አህመድ ሙሉ ፍቃድ ወደሥልጣን የተመለሰው የሕወሃት ቡድን አሰፍስፎ ጦሩን እየሰበቀ እያለ :

- የአብይ መንግስት ኦነግ ሸኔ እያለ በሚጠራው ጽንፈኛ ታጣቂ ቡድንና : በነሽመልስ አብዲሳ በሚታዘዙ እጅግ ጨካኝ ሕገ ወጥ ሚሊሽያዎች : በሌሎችም ግፈኞች ሲካሄድ የቆየውና አሁንም ያላባራው : በወለጋና በቤኒሻንጉል በመተከል በሌሎችም የሀገሪቱ አካባቢዎች : የአማራ ተወላጆችን ማሳደድና መጨፍጨፍ ባልቆመበት ሁኔታ :

- አልፎ ተርፎም በአዲስአበባና አካባቢው : የአማራ ተወላጆችንና ሌሎች ኦሮሞ ያልሆኑ ዜጎችን እየመረጡ : ቤታቸውን ላያቸው ላይ በግሬደር እየደረመሱ : በመቶ ሺዎች ማፈናቀልና : ከነሕፃናት ልጆቻቸው ጎዳና ላይ መወርወር በቀጠለበት ሁኔታ ፣ ይህ የግፍ ሥራ አንሶ : የአብይ ሰዎች በመንግስት ሚድያ ላይ በፊት ለፊት ወጥተው : ካለአንዳች ቅንጣት ሰብአዊነትና ሃፍረት: እነዚህን ዜጎች "ሕጋዊ ድሃ አድርገናቸዋል" እያሉ በሕዝብ መከራ ላይ እየተሳለቁ ባለበት ሁኔታ:

- የአማራ ተወላጅ የሆኑ ባለሀብቶችን ንብረትና ገንዘብ : ካላንዳች ሕጋዊ ምክንያት ማገድ በቀጠለበት ሁኔታ :

- የአማራ ተወላጅ የሆኑ የሕብረተሰብ አንቂዎችን ፡ መምህራንን የመንግስት ሰራተኞን ወጣቶችን ፡ ከመንገድ ላይና ከቤታቸው በግፍ ማፈንና መሰወር መደብደብ ማሰቃየት መግደል በቀጠለበት ሁኔታ ፡

- በአዲስአበባና በሌሎችም ቦታዎች ፡ የአማራ ተወላጆችንና ሌሎችንም ከመንገድ ላይ እያፈኑ ፡ ቤተሰቦቻቸው ከአቅም በላይ የሆነ ቤዛ/Ransom ንብረታቸውን ሸጠውም ቢሆን እንዲከፍሉ ማስገደድ ፡ መክፈል ካልቻሉም ፡ የታገቱትን በአሰቃቂ ሁኔታ መግደል እየተካሄደ እያለ ፡

- ከአማራ "ክልል" ወደ አዲስአበባ የሚመጡ የጭነትና መኪኖችን ፡ በነሽመልስ አብዲሳ ትእዛዝ እያገቱ አዲስአበባ እንዳይገቡ መከልከል ፡ ጭነታቸውን መዝረፍ ፡ የመንገደኛ አውቶብሶችን እያስቆሙ ፡ ለሕክምና የሚሄዱትን ጭምር አዲስአበባ እንዳይገቡ መከልከል ባልቆመበት ሁኔታ ፡

- መንግስት ተብዬው ፡ ይህንን በአማራ ሕዝብ ላይ በየቀኑ በሰፊው የሚካሄድ የግፍ ግፍ ፡ እንኳን ሊያስቆምና ለሕዝቡ የሕይወት ዋስትና ሊስጥ ቀርቶ ፡ ጨፍጫፊዎቹን በቀጥታም በተዘዋዋሪም እያባባለና እያገዘ ባለበት ሁኔታ ፡

- በአልጠግብ ባይነት የሀገራችንን ሕዝብ በገፍ የፈጁትና ያስፈጁት የሕወሃት መሪዎችና የጦር አዛዦች ፡ በአብይ መንግስት ሲሳሙና ሲሸለሙ ፡ በአንፃሩ እነሱን በጀግንነት የመከቱትና ሀገራቸውንና የአብይን መንግስት ከመፈራረስ ያዳኑት ፡ እንደነ ጄኔራል ተፈራ ማሞ ያሉ የኢትዮጵያ የቁርጥ ቀን ልጆች ፡ በአብይ አህመድ ትእዛዝ ሕክምና ተከልክለው ሞት ተፈርዶባቸው እያሉ ፡

- "የአማራ ክልል መንግስት/የአማራ ብልፅግና" የሚባሉት ህሊና ቢስ ሆድ አደር የአሽከርነት ሱሰኞች ፡ ሠላሳ ሁለት አመት ሙሉ ሕዝባቸውን ሲያስቀጠቅጡና ሲቀጠቅጡ ኖረው ፡ አሁን እንኳንስ የአማራን ሕዝብ ሊታደጉ ቀርቶ ፡ ዛሬም እንደገና ከአዲሶቹ ጌቶቻቸው ሥር ተኮልኩለው ፡ የአማራን ሕዝብ አስገዳይና ገዳይ ሆነው በተሰለፉበት ሁኔታ ፡

- የአማራ ሕዝብ ፡ በምዕራብ በሱዳን የድንበር ተሻጋሪ ወታደሮች ፡ በምስራቅ በሕወሃት ፡ በደቡብ በተለያዩ በኦሮሞና በሌሎች ጎሳዎች ስም በተደራጁ ታጣቂዎች የሚደርስበት ጥቃትና የሕልውና ፈተና ሳይቀረፍና ፡ ምንም ግልፅ የሆነ መተማመኛ ሳይኖረው ፡

- መንግስት ለሕዝቡ በሕይወት የመኖር ዋስትና ለመስጠት ባልቻለበትና ፡ በተቃራኒው ከጨፍጫፊዎቹ ጋር በሚያብርበትና ራሱ የሕዝብ ጨፍጫፊ በሆነበት ሁኔታ ፡

- ሕግ ማክበርና ፍትህ የሚባል ነገር ፡ በቀዳሚነት መንግስት ነኝ በሚለው ሕገወጥ ቡድን ተሸቀንጥሮ በተጣለበት ሁኔታ ፡

ይህ ሁሉ ከላይ የተዘረዘዉ ግፍ ባልቆመበትና ፡ የአማራ ሕዝብ ወደ ፈጣሪው እግዚኦ ከማለት ሌላ ምንም አይነት ከለላ ባላገኘበት አውድ ፡ በሰላም አርፎ የተቀመጠውና በመንግስት ላይ አንድም ጥይት ተኩሶ የማያውቀው ፡ ይልቁንም ውድ ሕይወቱን እየሰዋ የመንግስት አጋር ሆኖ የከረመው የአማራ ፋኖ ሕዝባዊ ኃይል ፡ ለምንድን ነው ከሌሎች አማራን በጠላትነት ከሚፈርጁና ከሚፈጁ የታጠቁ ኃይሎች በፊት በግድ ትጥቅህን ፍታ የሚባለው??

መንግስት ተብዬው ፡ ትናንት የሀገራችንን ሕዝብ በግፍ ከፈጁት ካስፈጁትና በሰላማዊ ሕዝብ ላይ ያን ሁሉ ዘግናኝ ወንጀል ከፈፀሙት ሕወሃቶች ጋር ፡ እንዲሁም ኦነግ ሸኔ ከሚባሉት ራሱ አሸባሪ ብሎ ከፈረጃቸው ሰላማዊ ሕዝብ የሚፈጁ ሽምቅ ተዋጊዎች ጋር ለሰላም ድርድር ሲቀመጥ፡ ለምንድን ነው አርፎ የተቀመጠውን የፋኖን ሕዝባዊ ኃይል ፡ በአግባቡ ለማነጋገርና በትእግስት ለመወያየት ያልፈለገውና ዘሎ ጦርነት ውስጥ የገባው??

ለምንድን ነው ለአማራ ሕዝብ የእባካችሁ አትግደሉን አታሳዱን በገዛ ሀገራችን መድረሻ አታሳጡን ፡ ሌላው ሁሉ ይቅርና በሕይወት የመኖር መብት ይኑረን ጥያቄ ፡ መልስ ለመስጠት ያልቻለው ወይም ያልፈለገው??

መልሱ ቀላልና ግልፅ ነው ፡ በተዘዋዋሪም በቀጥታም በመንግስት ሥልጣን ላይ ባሉ ቱባዎችም በጋሻ ጃግሬዎቻቸውም በንግግርም በተግባርም በየቀኑ እየታየ ነው ።

**አላማቸውና ተግባራቸው ፡ አማራ የሚባለውን መከረኛ ሕዝብ የምንችለውን በየሰበቡ ፈጅተን ፡ የተቀረውን "ሰብረን" አንገቱን አስደፍተን ፡ ሁለተኛ ቀና እንዳይል በሁሉም መስክ አድቅቀን ፡ ታሪኩንና ቅርሱን አውድመን ካልሆነ በስተቀር ፡ በኢትዮጵያ ምድር ላይ የ"ኦሮሙማ" እና "የኩሽ" የበላይነትና ፈላጭ ቆራጭነትን ለዘለቄታው ማስፈን አንችልም የሚል የሰይጣን ተልእኮ ነው ፡ እቅጩ ይኸው ነው ።**

ይህንን ተልእኮ ለማስፈፀም ፡ በአብይ አህመድና በአሽከሮቹ ክፉ አስተሳሰብ ፡ ለዚህ እርኩስ አላማ አልንበረከክም እምቢኝ አሻፈረኝ እንደሚል የሚታወቀውን የፋኖን ሕዝባዊ ግንባር ፡ ድምጥማጡን ማጥፋትና ፡ የአማራን ሕዝብ በሙሉ ማሽመድመድ ያስፈልጋል ።

ይኸው ነው ያሁኑ ጦርነት ብቸኛ አላማ ፡ ሌላው የአብይ መንጋዎች ልፍለፋ ፡ መሬት ጠብ የማይል ከንቱ መቀላመድና ፡ በግልፅ በአይን የሚታየውን እውነት መካድ ፡ ወይም እንደ ሰጎኗ ጭንቅላትን አሸዋ ውስጥ መቅበር ነው ።

**ሰላማዊና ኢትዮጵያዊ ኦሮሞ ወገኖቻችንን ጨምሮ ፡ ማናቸውም የኢትዮጵያ ብሄረሰቦችና ዜጎች ፡ ይህንን ሀገር አውዳሚ አላማ በፍፁም አይጋሩም ። የሁሉም ሕዝብና ዜጋ ፍላጎት ፡ ከወገኑ ጋር በሰላም በእኩልነት መኖርና ኑሮውን በሕብረት ማሻሻል ነው ።**

እነዚህ ክፉዎችና ጨካኞች : እንኳንስ አርባ ሚልዮን አማራ ቀርቶ : ስድስት ሚልዮን ትግራዋይ እንደ ሕዝብ ካበረና እምቢ ካለ : በምንም አይነት ማሸነፍ እንደማይቻል : ትናንት እነሱ ራሳቸው ከዋሉበት አውድ መማር የማይችሉ ደካሞች ናቸው ::

የዚህ ሁሉ እብደት ውጤቱ : አብይ አህመድና አሽከሮቹ በቀጣጠሉት እሳት : ራሳቸውንና ሀገራችንን ማጋየት ብቻ ነው ::

ይህንን ፍፁም የለየለት Genocidal ዓላማና ተግባር ለመመከትና : ኢትዮጵያን ከሀገራዊ ውድመት ለማዳን : ኢትዮጵያዊ የሆነ ሰው ብቻ ሳይሆን : ማንኛውም ሰብአዊ ፍጡር በሚችለው አቅምና መስክ መታገል ይጠበቅበታል ::

ከኦሮሞ ወገኖቻችን መሀል : በነአብይ አህመድ በነሽመልስ አብዲሳና በመሰሎቻቸው ቅጥፈት : ከንቱ ዲስኩርና ቅዠት የተታለሉና : በአማራም ሆነ በሌሎች ብሄረሰቦች መገፋት እንጠቀማለን ብለው የሚያስቡ ወገኖች ካሉ ፤ ሕውሃትን የሙጥኝ እንዲል ተወናብዶና ተገዶ : ግፍና መከራ ብቻ ካተረፈው ከትግራይ ሕዝብ መማር ይችላሉ : ያም አልበቃ ካለ **:** ***<u>ይህንን</u>*** ጥርት ያለ መልእክት አጢነው ራሳቸውን እንደገና መመርመር ይኖርባቸዋል ::

ለሁሉም የሀገራችን ዜጎች ፍትህና ርትእ የሚሹና : ለዚህም የሚታገሉ ኦሮሞ ኢትዮጵያውያን ወገኖቻችን በርካታ ናቸው : ሰፊው የኦሮሞ ሕዝብም ከዚህ የተለየ ፍላጎት የለውም ::

በአብይ አህመድ የአምስት አመት የሥልጣን ዘመን : በሰላምና በምቾት የሚኖር አንድም የሀገራችን ክፍል ወይም ብሄረሰብ የለም : ኦሮሞ ወገኖቻችንን ጨምሮ ሁሉም ፍዳውን እያየ ነው ::

ይህንን መከረኛ ሕዝብና ሀገር ለመታደግ ምንም ሌላ ምርጫ በማጣቸው ምክንያት : ግንባራቸውን ለጥይት ሰጥተው እየተዋደቁ ያሉትን : የሀገራችን የቁርጥ ቀን ልጆች የሆኑትን የፋኖ አርበኞችንና : ሌሎችም ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ፍትህና ርትእ የሚታገሉ ወገኖችን : በሚቻለው መንገድ ሁሉ መደገፍ : ባለን አቅም ሁሉ ደጀን መሆን : የዚህን እብድ ሰውዬ እርኩስ አላማና ሰይጣናዊ ተግባር : ባለን አቅም ሁሉ በአለም አቀፍ ደረጃ ማጋለጥና መሞገት : አማራጭ የሌለው ጉዳይ የሆነበት ግዜ ላይ ነው ያለነው ::

የሀገሪቱ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት : የአብይ አህመድ መንግስት ካለፉት አራት ወራት ጀምሮ በመላው የአማራ ሕዝብ ላይ በግልፅ እያካሄደ ያለውን Genocidal ጭፍጨፋ : በ"አስቸኳይ ግዜ አዋጅ" ስም እንዲያፀድቅ በታዘዘበት ግዜ : ቀደም ሲል የአብይ መንግስት የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር የነበሩት የሕዝብ እንደራሴ አቶ ገዱ አንዳርጋቸው ባደረጉት ንግግር : "ፓለቲካዊ ችግር በጠመንጃ ሊፈታ አይችልም : የችግሩ ምንጭ የ"ብልፅግና" መንግስት የፓለቲካዊ አመራር ውድቀት ነው : ይህ መንግስት እንኳን የአማራን ሕዝብ የማያባራ መፈናቀልና መገደል ሊያስቆም : ለችግሩ የተዛቡ አመለካከቶችን በማራመድ እያባባሰው ነው : የሀገር መከላከያ ሠራዊት በአስቸኳይ ጦርነቱን አቁሞ

ወደ ካምፑ መመለስ አለበት ፡ በአማራ ሕዝብና በ"ብልፅግና" ፓርቲ መካከል ያለው ግንኙነት በማይጠገን ሁኔታ ስለተበጠሰ ፡ ሁሉንም የአማራ ኃይሎች የሚያካትት ጊዜያዊ አስተዳደር ሊቋቋም ይገባል.." ብለው በጥብቅ አሳስበዋል ።

የአቶ ገዱ አስተያየት ለግዜው መሸጋገሪያ ሃሳብ ቢሆንም ፡ ዘላቂ ሀገራዊ መፍትሄ አይሆንም ።

**አሁን እየተካሄደ ባለው የዘር ፍጅት ምክንያት ፡ የአማራን ሕዝብ ከነዚህ አረመኔዎች ማዳን ቅድሚያ የሚሰጠው አንገብጋቢ ጉዳይ ሆኖ ሳለ ፡ በውስጡ ያዘለው ሀገራዊ አጀንዳና መዳረሻ አለ ፡ ይኸውም ኢትዮጵያን እንደሀገር ከመበታተንና ሕዝቡንም ከመተላለቅ ማዳን ነው ።**

**ይህ አደጋ ግምታዊ ነገር ሳይሆን ፡ አፍጦ የመጣና የአብይ አህመድ እብደት ባንድ ወይም በሌላ መልኩ ካልተወገደ በእርግጥ የሚሆን ነገር ነው ።**

የአማራ ፋኖ ሕዝባዊ ኃይል ፡ ራሱንና የአማራን ሕዝብ ፡ አልፎም የኢትዮጵያን ሕዝብ ከአብይ አህመድ ፡ ብርሃኑ ጁላ ፡ ሽመልስ አብዲሳ ፡ አበባው ታደሰ... ወዘተ የሚባሉ አረመኔዎች ጭፍጨፋ ለመከላከል በታላቅ ጀግንነት እየተፋለመ ነው ።

በዚህ እንደገና ሳይፈለግ በግድ ሕዝባችን ላይ በተጣለ የጦርነት ፍዳ ፡ የአብይ ጦር ገሚሱ ይዋጋል ገሚሱ የገዛ ወገኔን አልገድልም ብሎ ይከዳል ፡ ሌላው ደግሞ ሰላማዊውን ሕዝብ በአረመኔያዊ ጭካኔ ይጨፈጭፋል ።

የፋኖ ሕዝባዊ ኃይል የውጊያ አቅም እሱ ከጠበቀው በላይ ሲያይልበትና መከላከያ ውስጥም መሸብረክ ሲፈጠር ፡ የራሱ እብደት አንሶ ፡ የኦሮሞን ወጣቶች በሰፊው እየመለመለ ፡ ትናንት የኦሮሞ ደም ደማችን ነው ብሎ ከጎናቸው ተሰልፎ በታገለው ፋኖ እና ፡ በወገናቸው በአማራ ሕዝብ ላይ ለማዝመትና ፡ የባሰ የሕዝብ ለሕዝብ እልቂት ለማቀጣጠል በይፋ እየጣረ ነው ።

የፈሪነት የደንቆሮነት እና እጅግ ሥር የሰደደ ክፉነት መጨረሻው ይህ ነው ።

በዚህ እጅግ አሳዛኝ ፡ ሕዝብና ሀገር አውዳሚ የሆነ ወቅት ፡ ኦሮሞ ወገኖቻችንና ሌሎችም ብሄረሰቦች ፡ "የአማራ ደም የኛም ደም ነው" ብለው ፡ ሀገራቸውንና እና ሕዝባቸውን ከነዚህ አረመኔዎች ለማዳን አጋርነታቸውን እንደሚያሳዩ ይጠበቃል ።

**በአማራ ሕዝብ ላይ በሰፊው እየተካሄደ ካለው ጭፍጨፋ ባሻገር ፡ አዲስአበባን በግድ መሰልቀጥ ፡ የጉራጌን ሕዝብ አዋክቦ ወደ "ኦሮሚያ" መጨፍለቅ ፡ የደቡብ ኢትዮጵያ ሕዝብ እንዳያብር አስር ቦታ ሰነጣጥቆ የነሱ አሽከር ማድረግ ፡ የአፋርና የሶማሌን ክፍለሀገሮች መደፍጠጥ ፡ የ"ኦሮሚያ"ን ወሰን በሁሉም አቅጣጫ በግድ ማስፋፋት ፡ በሚሊተሪና ሴኩሪቲ ተቋማት ፡ በመንግስት መስሪያ ቤቶች በባንኮችና ፡ በሁሉም የኢኮኖሚና**

**የመንግስት ፖሊሲ አውታር በሆኑ ቁልፍ የአመራር ቦታዎች ላይ : ባለሙያዎቹን እያባረሩ ችሎታ ባይኖራቸውም ለአብይ ቡድን ታማኝ በሆኑ ባለግዜዎች መተካትና ተቋማቱን መቆጣጠር ፤ የ"ኦሮሙማ" የበላይ ፈላጭ ቆራጭነትን ማረጋገጫ እቅዶችና በተግባር ለማዋል እየተሞከሩ ያሉ ኩነቶች ናቸው ::**

**አብይ አህመድ ሀገራችን ኢትዮጵያን ገደል ለመክተት በከፍተኛ ፍጥነት እየተንደረደረ ነው:** በመጀመሪያው የሥልጣን አመቱ ፍፁም አፈቅቤ ሆኖ ቀርቦ : አብዛኛውን ኢትዮጵያዊ እሱ ራሱ በማያምንበት ስብከት አታሏል ::

ባለፈው አራት አመት ግን ሀገር አጥፊ አጀንዳው ነጥሮ ወጥቷል :: በታውከ አእምሮ የሚነዳ እጅግ አደገኛ ሰው መሆኑና: አይን ያወጣ ውሸታም አታላይ ዘባራቂ እጅግ ክፉ ሰው መሆኑ ገሃድ ወጥቷል::

ሰብአዊነት እውነት ቅንነት ደግነት ሀዘኔታ ሃፍረት ፀፀት ማስተዋል ብስለት ከስህተት መማር ከሚባሉት መሰረታዊ የሰው ልጅ እሴቶች : ከአንዳቸውም ጋር በጭራሽ አይተዋወቅም ::

"በእርግጠኝነት ልንገራችሁ : በድጋሚ ላለረጋግጥላችሁ” ወዘተ እያለ : ለመላዉ የኢትዮጵያ ሕዝብ በተደጋጋሚ ከገባዉ ቃል ውስጥ : በአፍጢሙ ያልደፋውና በተቃራኒው ያልሄደበት አንድም ሃገራዊ ጉዳይ የለም :: ከቅጥፈቱ ብዛት አንዱ ውሸት ሌላውን ጠልፎ እየጣለ የኮሜዲያኖች መቀለጃ ከሆነ ከርሟል ::

የለየለት Narcissistic Psychopath ከመሆኑ ብዛት : አምስት አመት ሙሉ ባለማቋረጥ እየተካሄደ ባለው የሺዎች ንፁሃን ድሃ ዜጎችና ሕፃናት የማያባራ አሰቃቂ እልቂት : እንኳን እንደሰው ፍጡር ሊያዝንና እንደ መንግስት መሪ ተገቢውን እርምጃ ሊወስድ ቀርቶ : ፓርላማ ውስጥ ተቀምጦ “እኔ የመንደር ጠባቂ ፓሊስ አይደለሁም : ገና ብዙ ሰው ይሞታል : አሜሪካም ሰው ይገደላል...” ወዘተ እያለ : በሀገርና በንፁሃን ዜጎች እልቂት ላይ በይፋ ያላግጣል ::

በመላው ሀገር ከአምስት ሚልዮን በላይ ድሃ ኢትዮጵያውያን ዜጎች በግፍ ከቀያቸው ተፈናቅለዉ : በየግዜያዊ መጠለያውና በየጫካው እየተሰቃዩና እየተንቀጠቀጡ እያሉ : እነሱን መልሶ ማቋቋም ቀርቶ : ይባስ ብሎ : በአዲስአበባ ዙርያ ዘራቸው እየተመረጠ የዜግነት መብታቸው የተገፈፈ ከመቶ ሺህ በላይ ቤተሰቦችን : በአማካይ አምስት መቶ ሺህ ዜጎችን : በአረመኔያዊ ጭካኔ መኖሪያ ቤታቸውን ላያቸው ላይ በግሬደር አስደርምሶ : ከነሕፃናት ልጆቻቸው መንገድ ላይ ወርውሮ : በብዙ ቢልዮን ዶላር ወጪ አዲስ ከተማና ቤተመንግስት ያስገነባል ::

ይህ ሁሉ ሕዝብ እንደዚህ እየተሰቃየ : የተቀረውም በየቀኑ እየናረ በሚሄደው የኑሮ ውድነት ክፉኛ እየተቸገረ ባለበት ወቅት : ለትርፍ ቤተመንግስት ይህን ያህል ገንዘብ ማውጣት ተገቢ ነው ወይ ተብሎ በሕዝብ እንደራሴዎች ሲጠየቅ : አያገባችሁም ገና ምን አይታችሁ : ለዚህ የቅንጦት ስራ እንዲያውም አምስት መቶ ቢልዮን ብር ነው የማፈሰው ብሎ እብደቱን በአደባባይ ያጋልጣል ::

ይህ ሁሉ ጉድ አልበቃው ብሎ : በሀገሪቱ ፓርላማ ውስጥ አይኑን አፍጥጦ "አዲስአበባ ዉስጥ ብዙ ኦሮሞ ጠል የሆኑ ሰዎች አሉ" እያለ : የኢትዮጵያዊ አብሮነት አክሊል የሆነው የአዲስአበባ ሕዝብ ላይ እልቂት ይጋብዛል :: የሀገር መሪ ነኝ የሚል ሰው ቀርቶ : ማንም ትንሽ ማሰብ የሚችል የሰው ፍጡር : እንዲህ ያለ ፀያፍና እጅግ አደገኛ ነገር እንኳን ፓርላማ ውስጥ የትም ቦታ አይናገርም ::

ሕግና ስርዓት የሚከበርበት መንግስት ቢኖር ኖሮ : አብይ አህመድ ሕዝብን በሕዝብ ላይ በማነሳሳት ተከሶ ዘብጥያ መውረድ ነበረበት :: እንዲህ ያሉ ተጠያቂነት የሌለባቸው የጥላቻ ዲስኩሮች ናቸው ሕዝብ እያጫረሱ ሀገራችንን ገደል እየከተቱ ያሉት ::

በተቃራኒው : ጥላቻ ይቅር ሰብአዊ መብትና ሕግ ይከበር ሕዝብ በከንቱ አይሰቃይ አይገደል የሚሉ ሰላማዊ ዜጎች : በስፋት ይሰደዳሉ ይታፈናሉ ይቀጠቀጣሉ ይገደላሉ :: በፓርላማ የሕዝብ እንደራሴዎችን ጨምሮ : በአብይ መንግስት ላይ በእውነት ላይ የተመሰረተ ትችት የሚያቀርቡ ዜጎች : ከያሉበት እየተለቀሙ በየማጎርያው ይሰቃያሉ ::

የአዲስ አበባ ነዋሪ የሆኑ በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ወጣት ወንዶችና ሴቶች : በመታወቂያ ወረቀታቸው ወይም በስማቸው አማራ መሆናቸው እንደ ወንጀል ተቆጥሮባቸው : ከየመንገዱ እየታፈሱ ራቅ ወዳሉ ማጎሪያዎች (concentration camps) እየተጋዙና እየታመቁ : በረሃብና በተስቦ በሽታ አበሳቸውን እያዩ ነው : አንዳንዶቹም እየሞቱ ነው ::

የኢትዮጵያን ሕዝብ ከዳር እስከዳር አስተባብረው : ታላቁን የአድዋ ድል የመሩት የኤፄ ምኒልክ መታሰቢያ ሐውልትና አደባባይ ዙርያ : አመታዊውን የአድዋ ድል በአል ለማክበር የተሰበሰቡ ዜጎችን : እየቀጠቀጡ ማባረር ሳይበቃቸው : በአቅራቢያው የሚገኘው ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተክርስትያን ውስጥ ድረስ ተከትለው ገብተው : በቲርጋዝና በጥይት ደብድበዋቸዋል ::

ለ"ኦሮሙማ" አዲስአበባን የመሰልቀጥ እኩይ አላማ ሲባል : በፍፁም ሕገወጥነት ካለቦታቸው አዲስአበባ ውስጥ በብዛት የተሰማሩት የ"ኦሮሚያ" ፖሊሶች : በበዓላት ቀን የኢትዮጵያ ባንዲራ ጥለቱ ላይ ያለበት ነጠላ ሽሚዝ ወይም ቲሸርት የለበሱ ዜጎችን : በአደባባይ እያስወለቁ ባንዲራውን እየቀደዱ ሲጥሉና ሰዉን ሲደበድቡ ማየት የተለመደ ሆኗል ::

የምስጋና በአል በሆነው በቅርቡ በተከበረው የእሬቻ በአል ላይ : የሽመልስ አብዲሳ ኮልኮሌዎች በብዛት ሆነው : **" በአዲስአበባ በአዳማ በቢሾፍቱ...ወዘተ የምትኖሩ አማሮች : <u>ፋኖን ካላወገዛችሁ በናንተ ላይ ይብሳል</u> : አዲስአበባ የኦሮሞ ነው" እያሉ በአደባባይ እየጨሁ የጄኖሳይድ ደወል ሲያሰሙ ነበር** ::

ይህ የፍጅት ጥሪ የመነጨው ከአብይና ከሽመልስ ጎራ ስለመሆኑ አንዱ ማሳያ : በዚህ ቀውጢ ሰአት እንዲህ ያለ እጅግ አደገኛ ነገር በይፋ በአደባባይ ሲለፈፍ : መንግስት ተብዬዎቹ ለይስሙላ እንኳን

ይህ ልክ አይደለም ብለው አንዷት መስመር ለመናገርና : ሕዝቡን ትንሽም ቢሆን ከሽብር ለማረጋጋት አለመፈለጋቸው ነው ::

**ሩዋንዳ ውስጥ ከሶስት ወራት ባልበለጠ ግዜ ውስጥ : አንድ ሚልዮን ሕዝብ በገጀራ የተጨፈጨፈበት የጄኖሳይድ ደወል የተደወለው ልክ በዚህ ሁኔታ ነው** ::

በሀጫሉ ሁንዴሳ መገደል ሰበብ : ከጉዳዩ ጋር ምንም ግንኙነት የሌለው የሻሸመኔ ከተማ ሲቃጠል : ንፁሃን አማርኛ ተናጋሪዎችና ሌሎችም የኦርቶዶክስ ሃይማኖት ተከታዮች ከየቤታቸው እየተጎተቱ ሚስትና ልጆቻቸው ፊት እንደበግ ሲታረዱ ፤ የከተማው ከንቲባ ገዳዮቹን ለማስቆም አቅቶት እርዳታ ለመጠየቅ ለአለቃው ለሽመልስ አብዲሳ ቢደውል : “አርፈህ ተኛ” የሚል ትእዛዝ እንደተሰጠው በይፋ መመስከሩ የትናንት ክስተት ነው ::

ሽመልስ አብዲሳ ለዚህ ወንጀል እንኳን ተጠያቂ ሊሆን ቀርቶ : የአዲሳባን ሕዝብ በተመሳሳይ ሁኔታ ከገፋ በኋላ የሚንደላቀቅበት ቤተመንግስት “ፊንፊኔ” ውስጥ ለማስገንባት ሽር ጉድ እያለ ነው ::

**የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የሰብአዊ መብት ኮሚሽን : ከሩዋንዳው እልቂት አመጣጥና አካሄድ ተምረው : በዚህ ወር ባወጡት ዝርዝር ሪፖርት : ኢትዮጵያ ውስጥ ያለው ሰፊ የሰብአዊ መብት ቀውስና : እየተባባሰ ያለው ዘር ተኮር ጦርነት : ወደ ጄኖሳይድ እያመራ ነው ብለው በማያሻማ ቋንቋ በጥብቅ አሳስበዋል ::**

**ባሁኑ ሰዓት : የአብይ አህመድ ጦር በበርካታ የአማራ “ክልል” አካባቢዎች መብራት ስልክና ኢንተርኔት አጥፍቶ : ታዛቢ በሌለበት የፋኖን ሕዝባዊ ኃይል ለማሸነፍ እየሞከረና : ሰላማዊውን ሕዝብ በከባድ መሳርያ በድሮንና በአየር ኃይል : በየከተማውና በየማሳው ላይ እየፈጀ ነው ::**

ሀገሩ በከፍተኛ የጦርነት እሳት : በሰላማዊ ዜጎች ፍጅትና በአጠቃላይ ሁከት ክፉኛ እየተለበለበ ባለበት በዚህ እጅግ አስፈሪ ሰአት : አብይ አህመድ “ ግዜው ዳያስፖራ ኢትዮጵያውያን ወደ ሀገራቸው የሚመለሱበትና : ውጭ ሀገር ልጅ ማሳደግ ስለማይመች ሀገራቸው አምጥተው የሚያሳድጉበት ግዜ ነው…” እያለ : የሕፃን አይሉት የእብድ ነገር ይዘላብዳል ::

የአማራ ፋኖን ሕዝባዊ ኃይል እና የአማራን ሕዝብ እጨፈልቃለሁ ብሎ የከፈተው የእብሪት ጦርነት መልሶ ሲለበልበው : የሕዝቡን ቀልብ ለማስቀየስ የሚችል መስሎት : “ውሃ የባህር በር ቀይ ባህር ወዘተ” የሚል አሁን ባለንበት እጅግ ከፍተኛ ሀገራዊ ሁከትና እልቂት ወቅት ትርጉም የለሽ የሆነ ዝባዝንኬ ያወራል :: የመንግስትን ሥልጣን በሙሉ ጠቅልሎ በእጁ አስገብቶ : ይህን ሁሉ የማያቋርጥ የሕዝብ ፍጅትና ስቃይ በቀጥታ በግለሰብ ደረጃ እየመራ : በጎን ደግሞ ሃይማኖተኛ ነኝ እያለ ይቀባጥራል : የእግዜርን የአላህን ስም በሐኬት በከንቱ ሲጠራ ይውላል ::

**አብይ አህመድ በአንድ በኩል የገዛ ሕዝቡን በ"ሀገር መከላከያ" ሠራዊት በመጨፍጨፍ : በሌላ በኩል ደግሞ አዲስ የተንደላቀቀ ቤተመንግስት በማስገንባት ሌት ተቀን በተጠመደበት በዚህ የሀገራችን የጭንቅ ሰአት : በተባበሩት መንግስታት ሪፖርት መሰረት በድርቅ በጦርነትና በመፈናቀል ምክንያት <u>36 ሚልዮን</u> ኢትዮጵያውያን በረሃብ እየተሰቃዩ ይገኛሉ : በተቀረውም ሀገር ድህነት እየተባባሰ ነው : በከተማ የሚኖሩ ደሞዝተኞች በቂ ምግብ በልተው ለማደር እጅግ ተቸግረዋል :: በገንዘብ ሚኒስትሩ ሪፖርት መሰረት : በሰሜኑ ጦርነት ምክንያት በትግራይ በአማራና በአፋር የደረሰውን ውድመት መልሶ ለማቋቋም <u>ከ28 ቢልዮን ዶላር</u> በላይ ያስፈልጋል ::**

የአብይ አህመድ የ"ብልፅግና" መንግስት : በሁሉም መለኪያ ፍፁም የተበላሸ ሀገር አውዳሚ መንግስት መሆኑ ጥርት ብሎ እየታየ ነው :: በሀገሪቱ ዋና ዋና አጀንዳዎች በሙሉ ፤ በሕዝብ ሰላምና መረጋጋት : በኢኮኖሚ ማኔጅመንት : በሕግና ፍትህ : በሕዝብ አስተዳደር : በውጭ ፖሊሲና ዲፕሎማሲ : በሁሉም መስክ ሙሉ በሙሉ ውዳቂ ነው ::

**ጠቅላይሚኒስትር ነኝ ባዩ : በራሱም ሆነ በሌሎች ምክር ለመሻሻልና ስህተቱን ለማረም የሚያስችለው መሰረታዊ የአእምሮ ብቃትም ሆነ : ለሕዝብና ለሀገር የሚያስብ ልብ በጭራሽ የሌለው CERTIFIED PSYCHOPATH ነው ::**

**አብይ አህመድ : ነገ ዛሬ ሳይባል የመንግስት ሃላፊነቱን : በሀገር አቀፍ የምክክር ሸንጎ ለሚታቀፍ የሽግግር መንግስት ማስረከብ አለበት :: ኢትዮጵያን እንደሀገር ለማስቀጠልና ሕዝቡን አሁን ከሚታየው የባሰ እልቂት ለማዳን ምንም ሌላ አማራጭ የለም ::**

**በአንድ ወፈፌ አምባገነን ማን አለብኝነትና የጥፋት ውርጅብኝ : ኢትዮጵያን የሚያክል ሀገር ሊፈርስ አይገባም ::**

ኢትዮጵያዊነት ምን ግዜም አሸናፊ ነው :: ለማሸነፍ ግን : በመሰረታዊ ኢትዮጵያዊ አብሮነትና እኩልነት : በሕዝብ ሰላም እና የኑሮ መሻሻል ላይ የሚያተኩር : ጥርት ያለ ሀገራዊ እይታና የማይታጠፍ ፅናት ያስፈልጋል ::

ኢትዮጵያ : ማንም መደዴ ባለግዜ መሬት ጠብ በማይል አደንቋሪ ፖለቲካ እያፈረሰ እንደገና የሚያቦካት ሀገር መሆኗ : ላንዴና ለመጨረሻ ግዜ እንዲያበቃና ዳግም እንዳይመለስ : በሀገር አቀፍ የምክክር ሸንጎ በሚወለድ ፅኑ መሠረት ላይ መቆም አለባት ::

ሀገራችን ዝንተአለም የጦርነት አውድማ : ድሃና የፈረንጅ እርጥባን ለማኝ የሆነችው : ምንም ሀገር በቀል ሀብት ስለሌላት ወይም የሰነፍ ሕዝብ ሀገር ስለሆነች አይደለም :: ታሪኳም ቢሆን እንደሁሉም የአለም ሀገሮች ልማትም ጥፋትም ያለበት ነው :: ልማቱም ጥፋቱም ደግሞ የሁሉም ማህበረሰብ ድርሻ አለበት :: በኢትዮጵያ የሩቅም የቅርብም ታሪክ : አልሚ ብቻ ወይም አጥፊ ብቻ የሆነ ማህበረሰብ በጭራሽ ኖሮ አያውቅም ::

**ኢትዮጵያ የማያቋርጥ የድህነትና የጦርነት አውድማ የሆነችው ፡ በየወቅቱ የሚነሱ ባለግዜዎች ፡ መጥፎውን እያረሙ መልካሙን እያለመለሙ ፡ ኢትዮጵያዊ አብሮነት እና የሕዝብ ኑሮ መሻሻል ላይ ከማተኮር ይልቅ ፡ ለራሳቸው የማያዛልቅ ሥልጣን እና ዘረፋ እንዲመቻቸው ፡ ሕዝብን በአሰስ ገሰሱ ማናቆርን ቅድሚያ ስለሚሰጡ ነው ፡፡**

ባለፉት ሀምሳ አመታት ፡ በተለይም በወያኔ/ኢህአዴግ ዘመን ፡ ለጥቂቶች የስልጣንና የዘረፋ ፍላጎት መሳርያነት ሲባል ፡ ሀገሪቱ እንደ ሁሉም አገር ወጣ ገባ በሆነ የታሪክ ሂደት የተዋቀረችበትን ትርክት ፤ እውነቱንና መልካም ጎኑን ሆን ብሎ በመደበቅ ወይም በመካድ ፡ መጥፎውን በማጋነንና በፍፁም ሐሰት በአንድ ብሄረሰብ ላይ በመለጠፍ ፡ የሐሰት ትርክት በመጨመር ፡ በሌላው ሕብረተሰብ መንፈስ ውስጥ እጅግ የተለጠጠ የተበዳይነት የቂምና የጥላቻ መርዝ በመዝራት ፡ አንድ ሙሉ ትውልድ ለማያባራ ሁከት አዘጋጅተው ፡ ሀገርና ሕዝብ ፍዳቸውን እያዩ ነው ፡፡

ይህንን የጥፋት አዙሪት ለመግታት ፡ በሀገር አቀፍ የምክክር ሸንጎ ፤ የሁሉንም የሕብረተሰብ ክፍል መሰረታዊ ጥይቄዎች በሰፊ ትእግስት በሚገባ በማዳመጥ ፡ በእርቅ መንፈስ ፡ በማስተዋል በሐቅ በእውቀት ፡ ምርቱንና ግርዱን በጋራ በመለየት ፡ በሕዝባችን ዘላቂ ጥቅምና የኑሮ መሻሻል ፡ በእኩልነትና የአብሮነት እሴቶች ላይ በሚያተኩርና ፡ የሚያስፈልገውን ግዜ (ጥቂት አመታት) ወስዶ በሚደራደር ጉባኤ ወደ ጋራ ስምምነት (Grand Bargain) መድረስ ይቻላል ፡፡

ኢትዮጵያ ውብ ባህልና ቋንቋ ያላቸው የብዙ ድንቅ ብሄረሰቦች ሀገር መሆኗ የሚያነጋግር ነገር አይደለም ፡ በረጅሙ የሀገራችን የታሪክ ጉዞ ሕዝቡ በተለያየ ግዜና በተለያየ ምክንያት በየአቅጣጫው እየፈለሰ እየተጋመደ መኖሩም የሚያከራክር አይደለም ፡፡

የዛሬ 49 አመት በ1967 ዓ.ም የታወጀው የመሬት ላራሹ አዋጅና ፡ ከዚያም በኋላ የተደረጉት ለውጦች ፡ ከነግዙፍ ግድፈቶቻቸው ፡ ቢያንስ በሀገራችን ውስጥ በባላባት መጨቆንን ማስቀረታቸውና ፡ የብሄረሰቦችን ክብር ባህልና ቋንቋ ከፍ ማድረጋቸው እሙን ነው ፡፡ በዚህ ሂደት ግን ሆን ተብሎ አንድ ትውልድ ሙሉ የተዘራው ፡ በሐሰት ትርክት ላይ የተመሰረተ ጥላቻና ቂም ፡ ሀገራችንን ገደል እየከተተ ነው ፡፡

**ዜጎች በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ትምህርት እንዲማሩ እንዲተዳደሩና እንዲዳኙ ፡ ባህላቸውን እንዲያዳብሩ ፡ በየአካባቢያቸው የአስተዳደር እርከኖች ራስገዝ እንዲሆኑ ማድረግ ተገቢ ነው ፡፡ ይህንንም ለዘለቄታው ለማሳካት፡ ባለፉት ሠላሳ ሁለት አመታት የተኬደበትን ጉዞ ምርቱንና ግርዱን በቅንነት በመመዘን ፡ በሰፊ ብሔራዊ ውይይት ፡ ጥልቅ ጥናትና በሕዝብ ፍቃድ ላይ የተመሰረተ ፡ የተሻሻለ የፌዴራል ሥርአት አስፈላጊነት እንዳለ ሆኖ ፤ ኢትዮጵያችን ውስጥ ማናቸውም ዜጋ ፡ የትም ይወለድ የትም ይደግ ፡ ከየትኛውም ብሄረሰብ ይውጣ ፡ በሕጋዊ መንገድ ከያዘውና ግብር ከሚከፍልበት የግል ይዞታው ውጪ፡ በማናቸውም የኢትዮጵያ መሬት ላይ ፡ ከሌላው ኢትዮጵያዊ የተለየ መብትና ፡ ሌላውን ዜጋ አግላይና ገፊ የሆነ "ክልል" ሊኖረው አይገባም ፡፡**

የሁሉም ክፍለሀገሮች እና ብሄረሰቦች ውብ ባህልና ቋንቋ ማበብ : የተመጣጠነ የኢኮኖሚ እድገትና ተጠቃሚነት : በቀዳሚነት በዘር ላይ የተቀረቀረ አናቋሪና አጋዳይ ሕገመንግስት እና : በዘር ላይ ብቻ የተመሰረተ የ"ክልል" አጥር አያሻውም :: ዘር ከፖለቲካ መዋቅሩ ተወግዶ : የማመጣጠኑ ተግባር በኢኮኖሚ በትምህርት በባህልና ቋንቋ እድገት ፖሊሲዎች እንዲያውም በተሻለ ሊተገበር ይችላል :: ስኬታማ የሆኑ ሕብረብሄራዊ ሀገሮች ያደረጉት ይህንን ነው :: እኛ ሀገር የሰፈነው የዘረኝነት መርዝ በዚያ መልኩ ካልታረመ : መንገዱ ቁልቁለት ብቻ ነው ::

ሕብረብሄራዊ አብሮነትና እድገት በምኞትና በዲስኩር አይመጣም :: **"ዘፈኑ የፍቅር ኑሮው በዘር አጥር"** ይሳካል ብሎ ማመን : ያንኑ ቂጣ መላልሰው እየጋገሩ ጣእሙ ይቀየራል ብሎ እንደማመን ያለ "እብደት" ነው ::

ካሁን ወዲህ በኢትዮጵያ የመንግስት ሥልጣን ላይ የሚቀመጥ አካል : በኢትዮጵያዊ አብሮነት እና በሁሉም ብሄረሰቦችና ዜጎች እኩልነት : በሕዝብ ኑሮ መሻሻል : በሰላምና በሕግ የበላይነት ላይ የሚያተኩር መሆን አለበት ::

**ባለፉት ሃምሳ አመታት ሕዝባችንን ካለማቋረጥ ሲያወናብድና ሲያሰቃይ የኖረውን : የማንም እንኩቶ በየግዜው እየተነሳ የሚለፍፈውን : ሕዝቡን በሰበብ አስባብ የሚከፋፍል የሚያናቁርና የሚያደኸይ እኩይ ቡትቶ ፖለቲካን በቁርጠኝነት በቃ! በቃ! ለማለት ግዜው አሁን ነው ::**

**ሀገራችን ኢትዮጵያ : እንደ ሶማልያ ሶርያና የመን ሀገረ መንግስቷ ፈርሶ : 125 ሚልዮን ሕዝብ ሀገርና መንግስት የለሽ ሆኖ በሚልዮኖች የሚሰደድበት : የተቀረውም የማያባራ የእርስበርስ እልቂትና ስርዓት አልበኝነት (Anarchy) ውስጥ የሚገባበት አደጋ በግልፅ እየታየ ነው ::**

**ይህንን አደጋ ለመቀልበስ : ሁሉም ኢትዮጵያዊና ትውልደ ኢትዮጵያዊ : ከልብ መቆርቆርና ባለው አቅም ሀገሩን ለማዳን መታገል : ተደራጅተው የሚታገሉትን እውነተኛ የሕዝብ ወገኖች በጥንቃቄ እየለየ መደገፍ ይጠበቅበታል ::**

**እንደዚሁም : የሀገር መከላከያ ሠራዊት በአማራ ፋኖ ሕዝባዊ ኃይል ላይ በግድ የጫነውን አላስፈላጊ ጦርነትና : በአማራ ሕዝብ ላይ የሚያካሂደውን ፍጅት ካለምንም ቅድመ ሁኔታ ባስቸኳይ እንዲያቆም ከፍተኛ ድምፅ ማሰማት : ሁሉንም የሕብረተሰብ ክፍል ለሚያሳትፍ ሀገር አቀፍ የምክክር ሸንጎና ለሽግግር መንግስት የሚደረገውን ጥሪ መደገፍና ማገዝ እጅግ አስፈላጊ ነው ::**

**ከልክ በላይ መታገስ ውጤቱ ሀገር የለሽ መሆን ነው ::**

**---------- // ----------**